# በቤተሰብ ድጋፍ ማዕከላት ላይ ልዩ ትምህርት

ስለ ልዩ ትምህርት ጥያቄዎች አሉዎት? የአካል ጉዳተኝነት አገልግሎት መስጫ ስርዓትን በማሰስ ረገድ እርዳታ ያስፈልግዎታል? የሚቀጥለውን ሊሆን የሚችል እርምጃዎን ለይተው ለማወቅ እየተቸገሩ ነው?

The Parent Educational Advocacy Training Center (PEATC) Regional (የወላጅ የትምህርት አድቮኬሲ ማሰልጠኛ ማዕከል (PEATC) ክልላዊ) ለማገዝ እዚህ ይገኛል።

## PEATC ክላላዊ (PEATC Regional)

PEATC የቨርጂኒያ ፌዴራላዊ ኃላፊነት የተሰጠው የወላጆች ማሰልጠኛ እና መረጃ ማዕከል (PTI) ነው። PEATC በእርስዎ ግዛት ክልልውስጥ ሰራተኞች አሉት፣ እነርሱም የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን ለሚያገኙ የቨርጂኒያ ተማሪዎች ቤተሰቦች **ነፃ እና ሚስጥራዊ** እርዳታ ለመስጠት ዝግጁ ናቸው።



## የ PEATC Regional ልዩ ተግባራት

**PEATC Regional የቤተሰብ ድጋፍ ስፔሻሊስቶች፡-**

- የአካል ጉዳተኛ የሆኑ ልጆች ያሏቸውን ወላጆች ስለ አማራጮቻቸው፣ መፍትሔዎችን እንዲያመነጩ ለማስተማር፣ እንዲሁም ስለ ልጃቸው ልዩ የትምህርት አገልግሎት በቂ እውቀት ያላቸውን ውሳኔዎች እንዲያደርጉ ኃይል ለማስታጠቅ (በስልክ፣ በኢሜይል እና በአካል) ቀጥተኛ እርዳታን ይሰጣሉ።
- ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራሞችን (IEP) ይገመግማሉ እና ወላጆችን ለ IEP ስብሰባዎች፣ ለሽግግር ስብሰባዎች፣ እና ለብቁነት ስብሰባዎች እንዲዘጋጁ ያግዛሉ።
- አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚያስችሉ አማራጮችን ያብራራሉ እና ቤተሰቦች እያንዳንዱን ሂደት ውጤታማ በሆነ መንገድ ማዘጋጀትና ማሰስ እንዲችሉ ድጋፍ ይሰጣሉ።
- የቤተሰቦችን እና አብረዋቸው የሚሰሩ ባለሙያዎችን ዕውቀት ለማጎልበት በልዩ ትምህርት ተያያዥ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ስልጠና (በአካል እና በርቀት) ይሰጣሉ።
- የአካል ጉዳተኛ የሆኑ ተማሪዎች የትምህርት አገልግሎቶችን በተመለከተ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ በንቃት እንዲሳተፉ እና ስለ ህይወታቸው ውሳኔ እንዲያደርጉ የሚያስችሏቸውን የራስ ጥብቅና ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ ይረዳሉ።
- ከ 2-22 ዓመት እድሜ ያላቸው ልጆች እና ወጣት ጎልማሶች እንዲሁም የቤተሰብ አባሎቻቸውን ፍላጎት በተሻለ ሁኔታ እንዲያሟሉ ለማገዝ የግዛት እና የፌደራል ልዩ ትምህርት አቅርቦቶች፣ ችግሮችን የመፍታት እድሎችን እና ድጋፎችን ለቤተሰቦች ያቀርባሉ።
- በክልላቸው ውስጥ በትምህርት ቤት ምድቡ ከተሰየሙት ወላጆች እና የቤተሰብ አገናኚዎች ጋር ይገናኛሉ እና የትብብር ግንኙነቶችን እና የቅንጅት ሂደቶችን ያዳብራሉ።
- በትምህርት ቤት ምድቡ ከተሰየመው ወላጅ እና የቤተሰብ አገናኚዎች ጋር በመሆን የትምህርት ስልጠናዎችን ማቀድ እና ተግባራዊ ማድረግን፣ በአገልግሎት የመድረስ ስራን (outreach)፣ እና ለቤተስቦች ሌሎች ዝግጅቶችን ጨምሮ ስለ ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች የቤተሰብ ስጋቶችን ለመፍታት ይሰራሉ።


Virginia Department of Education
ልዩ ትምህርት ለቤተሰቦች

PEATC REGIONAL
partners@peatc.org
(703) 923-0010 or (800) 869-6782
እርዳታ በ 300+ ቋንቋዎች ይገኛል


Virginia Department of Education

peatc